# አስቸኮይ! በነፃ የኖርዌጅያን  ቋዋንቋእና  የኖርዊጂያን ማህበረሰብ መሰረታዊ እውቀት አስጨባጭ  ስልጠና

የነጻ የኖርዊጅያን ቋዋንቋእና የኖርዊጂያን ማህበረሰብ መሰረታዊ እውቀት ትምህርት የማግኘ መብት

በኖርዌ የሎት የመኖሪያ ፈቃድ በአጠቃላይ የ600 ሰዓትታት የነጻ ትምህርት የሚከተሉትን ለመማር መብት ይሰጣታል ፥

- የኖርዊጅያ  ቋዋንቋ (የ550 ሰዓትታት) እና
- የኖርዊጂያን ማህበረሰብ መሰረታዊ እውቀት የሚያስጨብጥ የ50 ሰዓታት ትምህርት

የትምህርት ስልጠናው በነፃ ሲሆን ተግባራዊ  የሚሆነው በመጀመሪያው ሶስት ዓመታት በኖርዊ ቆይታዎት ይሆኖል። ይህም የጊዜ ገደብ የሚጀምረው

- የመኖሪያ ፈቃድ ካገኙበትቀን ጀምሮ  ወይም
- ወደኖርዌ ህጋዊ የሆነ ፈቃድ ይዘው ከገቡበት ቀን ኣንስቶ ይሆናል

<u>**ማሳሰቢያ፥**</u> እላይ በተጠቀሱት የሶስት ዓመት ገደብ ውስጥ ስልጠናውን ካልጀመሩ ወይም የጀመሩትን ካላጠናቀቁ ትምህርቱን በራስዎ ወጭ መውሰድ ይኖርቦታል።

## የኖርዊጅያን ቋዋንቋእና የኖርዊጅያን ማህበረሰብ መሰረታዊ እውቀት አሰጨባጭ ትምህርት የመከታተል ግዴታ

የ600 ሰዓታት የኖርዊጅያን ቋዋንቋእና የኖርዊጅያን የማህበረሰብ መሰረታዊ እውቀት አሰጨባጭ ትምህርት ስልጠና የማጠናቀቅ ግዴታ ያለቦት

- ቀዋሚ የሆነ በኖርዌ የነዋሪነት ፈቃድ እና/ወይም
- የዜግነት መብት ለማገግኘት ማመልከቻ በሚያቀርቡበት ጊዜ እንዲፈቀድልዎት አስፈላጊ ስለሆነ ነው።

ከስልጠናው ግዴታ ነፃ ለመሆን ማመልከት  የሚችሉት

- የኖዊጅያን ቋዋንቋ ወይም የሳሚዎች ቋዋንቋ በቂ ችሎታ ያለዎት መሆኑን የሚያረጋግጥ ሰነድ ማቅረብ የሚችሉ ከሆነ ወይም
- የተለየ የጤና እክል ወይም  ሌላ ከበድ ያለ ኣሳማኝና በቂ ምክንያት ካለዎት ይሆናል።

## በተግባር ስለሚፈጸሙ ነገሮች መግለጫ

ስልጠናውን ለመውሰድ ወይም ከሰልሰጠናው ነጻ ለመሆን ማመልከት ከፈለጉ የህዝብ መመዝገቢያ ጽሕፈት ቤት ከተመዘገቡበት አውራጃ ወይም ኮሚውን ውስጥ ለሚገኘውን የጎልማሶች (አዋቂዎች ) ማሰለጥኛ ማእከል ማመለከቻ ማቅረብ ይኖርቦታል። በተጨማሪም በተጨማሪምማንኛውም ጥያቄ ካለዎት እንደዚሁም መብትን ወይም የጊዜ ገድቦችን የሚመለከት ጥያቂዎች ከአሎዎት ከዚሁ የጎልማሶች ማሰልጠኛ ማእከልን ማግኘት ይቻላል።

ተጨማሪ መረጃ ከፈለጉ ከሚከተሉት ድሕረ ገጾች መመልከት  ይችላሉ።

www.imdi.no  እና www.udi.no